# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 245 ጥር 16 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ወያኔ በሃይማኖታችን፣ በኑሮአችን ጣልቃ በመግባት እምነትን ለማዳከም የሚያደርገውን አፈናና ረገጣ እስከ መጨረሻው ታግለን በማስወገድ ዜጎች ካለምንም ጣልቃ ገብነት የእምነታቸው ነጻነት ይከበር ዘንድ አብረን ከእናንተ አባቶቻችን ጎን በመሰለፍ ትግሉን ወደፊት ለማድረግ እኛ የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላትና አመራር ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ ዛሬም ቆርጦ መነሳቱን በድጋሜ ቃል ይገባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዋልድባ መነኮሳትን ከፍተኛ ግፍና መከራ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ገለጹ

የጸለምት ወረዳ ባለስልጣናት፣ በዋልድባ ያለዘር ልዩነት ለዘመናት የኖሩ መነኮሳትን ትግሬ ካልሆናችሁ በዚህ ገዳም ውስጥ መኖር አትችሉም በማለት ከፍተኛ ግፍና መከራ እየፈጸሙባቸው መሆኑን ዘጋቢያችን መነኮሳቱ የጻፉትን አቤቱታ ዋቢ በማድረግ በላከልን ዘጋባ ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት መነኮሳቱ ለክልሉ የወያኔ ባለስልጣናትና ለሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በጻፉት አቤቱታ እንዳሉት ባለስልጣናቱ ግፍና በደል የሚፈጽሙባቸው በጣት የሚቆጠሩ የነሱን መነኮሳት፣የአካባቢውን ታጣቂዎችና ሚሊሺያዎች በመጠቀም ነው። በሃይማኖትም ሆነ በሀገሪቱ ህግ መንፈሳዊ ቦታ ማንም ያለዘር መድልዎ የሚገለገልበት ቦታ ቢሆንም እነርሱ ግን በማንነታቸው ምክንያት የዘር መድልዎ፣ እስራትና ድብደባ እየተፈጸመባቸው ነው - እንደ አቤት ባዮቹ መነኮሳት። ከዚህም ሌላ ከገዳሙ ውጪ በነጻነት ለመንቀሳቀስ የትግራይ ክልልን መታወቂያ የመያዝ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፤ የገዳሙ ማህተም ያለበትን መታወቂያ ይዘው ሲንቀሳቀሱ ይህ ተቀባይነት ስሌለው መንቀሳቀስ አትችሉም በማለት አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ ግፊት እየተደረገባቸው ነው።

በመሆኑም መነኮሳቱ ይህን አቤቱታ ለማቅረብ ወደ ጎንደር ሲጓዙ ቀጥታውን መንገድ በመተው የሁለት ቀን መንገድ ለመጨመርና በረሃ ለበረሃ ለመንከራተት ተገደዋል። ቀጥታውን መንገድ ለመጠቀም የመረጡትም ለእስር ተዳርገዋል።

በአቤቱታው እንደተገለጸው የደረሰባቸውን ግፍና በደል ለማሰማት የተንቀሳቀሱት መነኮሳት ሰላሳ አንድ ሲሆኑ፣ በርካቶች የዘርኝነት ጥቃቱ ሰለባዎች ገዳሙን በመልቀቅ ተሰደዋል። ባለስልጣናቱም መነኮሳቱን በማዋከብ፣ በመደብደብና በማሰር ከበታተኑ በኋላ ወደ ገዳሙ በመሄድ በማንአለብኝነት የራሳችን የሚሏቸውን ሰዎች በልዩ ልዩ የሃላፊነት ቦታ በመመደብ የገዳሙን ስርዓት አፋልሰው ሄደዋል ሲሉ አቤቱታ አቅራቢዎቹ አማረዋል።

በመጨረሻም በተደጋጋሚ በደረሰባቸው በደል፣ግፍና የዘረኝነት ጥቃት በገዳማቸው መኖር አለመቻላቸውን፣ የሌላ ሃገር ዜጋ ይመስል በገዛ ሃገራቸው በመንፈሳዊ በዓታቸው እንዳይኖሩ የማያውቁትን ፖለቲካ ተገን ባደረገ ዘረኛ አስተሳሰብ ህልውናቸው አደጋ ላይ መውደቁን በመግለጽ ይህ ችግር በእነርሱ ላይ ብቻ የሚቆም ባለመሆኑ ውሎ አድሮ ችግሩ ከመባባሱና ጠባሳ ከመተው በፊት የሚመለከታቸው አካላት አፋጣኝ መፍትሄ እንዲፈልጉ አሳስበዋል።

## ለከተማና ለአካባቢ ምርጫ ተብየው የተመዘገበዉ መራጭ 30 በመቶ ብቻ መሆኑ ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ በመጪዉ አመት በሚደረገዉ የከተማና የአካባቢ ምርጫ ተብየ ለመሳተፍ ተመዝግቧል ብሎ በመረጃ መልክ በሚሰጠዉ ቁጥርና በትክክል በምርጫዉ ለመሳተፍ በተመዘገበዉ ሰዉ ቁጥር መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች የምርጫ ቦርድ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። ወያኔ ከ89 በመቶ በላይ መራጭ ህዝብ እንደተመዘገበ በይፋ ቢያስታውቅም ይህ ዜና እስከደረሰን ድረስ በትክክል የተመዘገበው መራጭ ብዛት ከ33 በመቶ ብቻ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ወያኔ ካድሬዎቹንና በየወረዳዉ የሚገኙ አባላቱን የቤት ለቤት ቅስቀሳ እንዲያደርጉ በየቦታዉ የላከ ቢሆንም ህዝቡ ግን ወጥቶ ለመመዘገብ ፍላጎት አለማሳየቱ ታውቋል። በህዝቡ የምርጫ ፍላጎት ማጣት ግራ የተጋባው ወያኔ በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ የአመራር አባላቱን "ቀይ መብራት ውስጥ ናችሁ" የሚል ማስፈራሪያ በመላክ በክልል፤ በዞን፤ በከተማና በወረዳ ለሚገኙ ካድሬዎቹ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተደርጎ መራጩ ህዝብ ወጥቶ እንዲመዘገብ እንዲያደርጉ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላልፏል። ዘጋቢዎቻችን ያናገሯቸዉ ብዙ ሰዎች በምርጫው ለመሳተፍ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ገልጸዉ የወያኔ ካድሬዎች በየቀኑ ለምርጫዉ ተመዝገቡ እያሉ እንደሚጨቀጭቋቸዉና እንደሚያስፈራሯቸዉ ተናግረዋል።

## ኢትዮጵያ በወታደራዊ እንቅስቃሴዎች እየታመሰች ነዉ ተባለ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዳር አገርም ሆነ መሀል አገር በየቦታዉ የሚታየዉ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙ ወታደራዊ ምንጮቻችን ገለጹ። በተለይ የመለስ ዜናዊ ሞት ለህዝብ ይፋ ከሆነበት ግዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከደርግ ዘመን ወዲህ ታይቶ በማይታወቅ ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ እየታመሰች መሆኗን በየክልሉ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን የመከላከያ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ የላኩልን ዜና ያስረዳል።

ከሁለት ሳምንት በፊት ከ35 በላይ ታንኮችን የጫኑ ከባድ ተሽከርካሪዎች ወደ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍል የተጓዙ ሲሆን፣ ከአራት ቀን በፊት ደግሞ ከ30 ያላነሱ ታንኮች በከባድ ተሽከርካሪዎች ተጭነዉ ወደ ሰሜናዊዉ የአገራችን ክፍል ተጉዘዋል። ጠብ አጫሪዉ የወያኔ አገዛዝ የጦር መሳሪያዎችን ለምን በዚህ አይነት ፍጥነትና ብዛት እንደሚያንቀሳቅስ በትክክል ለማወቅ ባይቻልም በብዙ ምዕራባዉያንና የአገር ዉስጥ ወታደራዊ ጠበብቶች ግምት አገሪቱ ውስጥ በየክልሉ በሁሉም መስክ የሚታየው ህዝባዊ አመጽና አለመረጋጋት ወያኔን ክፉኛ ስላስደነገጠዉ ህዝባዊ እንቅስቃሴዉን በወታደራዊ ሀይል ለመቆጣጠር የታለመ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታናል። በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ስርዐቱን በትጥቅ ትግል የሚፋለሙ ሀይሎች በተለይ በቅርቡ የተቋቋመዉ እራሱን "የግንቦት ሰባት ሀይል" ብሎ የሚጠራዉ የተለያዩ ሀይሎች ስብስብ ወያኔን ክፉኛ እንዳስደነገጠዉ ብዙ ለአገዛዙ ቅርበት ያለቸዉ ምንጮች በመናገር ላይ ናቸዉ።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሙስሊሙ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ አንድ ስራ አስኪያጁን ማባረሩ ታወቀ

ከአየር መንገድ የውስጥ ምንጮች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሼባ ማይልስ እየተባለ የሚጠራውን ክፍል በስራ አስኪያጅነት ሲመሩ የነበሩትን አቶ አብዱል ጀባር ሀሚድን ከስራ ያባረረው የአየር መንገዱ ሙስሊም ሰራተኞች ከሌሎች ወገኖች ጎን ተቀላቅለው ተቃውአቸውን እንዲገልጹ አደራጅቷል በሚል ምክንያት መሆኑ ታውቋል። ስራ አስኪያጁ በአሁኑ ጊዜ በእስር ላይ እንደሚገኙ ታውቋል።

በተያየዘ ዜናም በሱፐርቫይዘርነት ደረጃ ስትሰራ የነበረችው ትእግስት ደምሴ ከስራ በተቀነሰ ሰራተኛ ላይ የሀሰት ምስክርነት እንድትሰጥ ተጠይቃ ፈቃደኛ ባለመሆና መሆኑ ታውቋል።

ኢሳት የኢህአዴግ አባል ለመሆን ፈቃደኛ ያልሆኑ 50 የአየር መንገዱ ሰራተኞች መባረራቸውንና በኢህአዴግ የወጣት ፎረም አባላት መተካታቸውን ገልጾ ነበር። ከስራ የተቀነሱት የ36 ሰራተኞች ሙሉ ስም ዝርዝር እና አሁን ያሉበት ደረጃ የደረሰን ሲሆን፣ ሙሉውን ዝርዝር በኢሳት ዌብሳይት ላይ ታትሞ መውጣቱን ለመግልጽ እንወዳለን።

በጉዳዩ ዙሪያ የአየር መንገዱን አመራሮች ለማግኘት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም።

## ፓሊሶች በአራት ኪሎ የሚገኙ ቤቶችን በእሳት አቃጠሉ

ለረጅም አመታት በአራት ኪሎ አካባቢ የኖሩ ሰዎች ቦታው ለሼራተን ሆቴል ማስፋፊያ ይፈለጋል በሚል ቤታቸውን ለቀው እንዲወጡ ሲነገራቸው እንደቆየ የተናገሩት አይን እማኞች፣ ነዋሪዎቹ በበኩላቸው መንግስት ተተኪ ቤት እስካልሰጣቸው ድረስ አካባቢውን ለቀው እንደማይሄዱ ሲከራከሩ ቆይተዋል። ዛሬ ጧት ወደ አካባቢው ያቀኑት ፖሊሶች ነዋሪዎቹ እቃዎቻቸውን ሳያወጡ በቤታቸው ላይ እሳት በመልቀቅ ቤታቸውን አቃጥለውባቸዋል። ነዋሪዎቹ በጩሀት ወደ ፓርላማ በመሄድ አቤት ቢሉም ሶስት ሰዎችን በመወከል ችግራቸውን እንዲያቀረቡ ተነግሮአቸዋል። ፖሊሶች ወደ አካባቢው በመድረስ ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩ ነዋሪዎችን አባረዋቸዋል።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ የአይን ምስክር ለኢሳት እንደገለጡት፣ ተማሪዎች ደብተራቸውን እንኳን ሳያወጡ ቤታቸው እንደተቃጠለባቸው፣ ብዙዎችም በከፋ ችግር ላይ መውደቃቸውን ገልጸዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የሃይማኖት መብቶች እንዲከበሩ ለሁሉም መብቶች የመታገያ ግዜው አሁን ነው!

ፍትህ፣ ነጻነት፣ እኩልነትና አንድነት የብዙ ሃይማኖቶች መሰረታዊ መርህ እሴቶች ናቸው። እነዚህ ቲውፊቶች ለአለፉት 20 አመታት በዘረኛው ወያኔ እየተሸረሸሩና እየመነመኑ ዛሬ ከእነ አካቴው በሀገራችን ኢትዮጵያ ስለመሰረታዊ የሰው ልጅች መብት ነጻነት እንዳይወራ፤ ወያኔ የጥይት አፈ ሙዞች በእያንዳንዱ የህዝብ አገልግሎት ተቋማት ላይ በመደቀን የአምልኮ ቦታዎችን ሳይቀር በመዳፈር ህዝበ ምእመናኑ የእኔ የራሴ የሚለው የአምልኮት ቦታ እና ህግ እንዲያጣና እንዳይኖረው እያደረገ ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀን ወደቀን እየተባባሰ የመጣው የእምነት ነጻነት እጦት ሁላችንንም ሊያሳስበን እና ሊያስተሳስረን የሚገባበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። በተለይም በታሪካችን፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በእምነት፣ በዘር፣ በፖለቲካ እስከ ቅርብ ጊዚያት ድረስ ሳይለያይ ተከባብሮና ተሳስቦ የሚኖር ህዝብ እንደሆነ የማይካድ ሃቅ ነው።

ይሁን እንጅ ከቅርብ ግዜ ወዲህ አምባገነኖች በፈጠሩት ህገ- አራዊት በሆነው የከፋፍለህ ግዛ እና የአንድ ዘር የበላይነት ፖሊሲ አማካኝነት የምንወዳት ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ አበው ለአንድነቷ፣ ለህልውናዋ የሞቱላት፣ ዘውግ፣ ቋንቋና የሃይማኖት ልዩነት ሳያግዳቸው የገነቧት እማማ ኢትዮጵያ፤ የልጆቿ የኤሎሄ ማሰሚያ ስፍራዎች፣ ተቋማትና የገዳማት አባቶች በህወሃት የጥፋት አለንጋ እየተገረፉ ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን 4ኛውን ፓትርያርክ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ከእምነቱ ቀኖና ህግ ውጭ በሆነ መንገድ ህጋዊውን ፓትርያርክ በማባረር በዘረኛው የወያኔ አስተዳደር ስርአት ውስጥ በማስገባት አባ ጳውሎስ እስከሞቱበት እለት ድረስ እና አሁንም ምእመናኑ በመከፋፈል የተሳካላቸው ወያኔዎች፤ በቅርቡ ሊደረግ የነበረውን የእርቀ ሰላም ሂደት በወያኔ ጀሌዎች እንዲሰናከል የስርአቱ አገልጋይ አባቶች የሆኑትን፤ ልሳናቸውን በመጠቀም የኦርቶዶክስ ተዋህዶን እምነት አሁንም በወያኔ ቁጥጥር ስር ሆና እንድትመራ የተደረገው አሳዛኝ ክስተት አንዱ ነው።

ወያኔ አንግቦ የተነሳው አላማ፤ ዜጎች በዜግነታቸው በሚኖሩበት ሀገር ምንም አይነት ነጻነት እንዳይሰማቸው፣ የጥቃት ሰለባዎች እንዲሆኑና የዜጎች የማምለክ ነጻነትን በማዋረድ ጸረ - ሐይማኖታዊ ተግባሩን እንደሙስሊሙ ማህበረሰባችን እና እንደተቀረው የህዝብ ተቋማት ሁሉ የደም እጁን በማስገባት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ብሄርተኝነትን በማራመድ የተለመደ የፖለቲካ ስራውን እየሰራ ነው፡፡

በአንጻሩ ስለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ቀን ከሌት የሚጸልዩትን አባቶች ደግሞ እንደጠላት በመፈረጅ ለእንግልትና ለስደት እያበቁ የእግዚያብሄርን ቤት የካድሬዎች ገዳም የፖለቲካ እድሜ ማራዘሚያ ማድረጋቸው ለህዝበ ምእመናኑ እና ለቤተክርስቲያኗ ነጻነት ክብር እና ደንታ እንደሌላቸው የሚያሳይ ሃላፊነት የጎደለው አምባገነናዊነት ነው።

ሰሞኑን ህጋዊው ሲኖዶስ ለህዝብ ይፋ በማድረግ ባወጣው መግለጫ፤ ሲኖዶሱ ለሀገራችን አንድነትና ሰላም ሲል የሞከረውን የእርቀ ሰላም ሂደት በማድነቅ፤ የወገናችሁ ጉዳይ አስጨንቋችሁ፣ አሳስቧችሁ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእምነት፣ በዘር፣ በጎሳና በፖለቲካ ሳይለያይ የሲቪሉም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች በመተባበር በዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ እንታገለው ዘንድ ያቀረባችሁትን ጥሪ ተቀብለን በማስተዋልና በጽናት ዘረኛውን ወያኔ እንታገለዋለን፡፡ ለዚህም ከእናንተ ጋር ሆነን ለድል እንደምንበቃ አንጠራጠርም።

ወያኔ በሃይማኖታችን፣ በኑሮአችን ጣልቃ በመግባት እምነትን ለማዳከም የሚያደርገውን አፈናና ረገጣ እስከ መጨረሻው ታግለን በማስወገድ ዜጎች ካለምንም ጣልቃ ገብነት የእምነታቸው ነጻነት ይከበር ዘንድ አብረን ከእናንተ አባቶቻችን ጎን በመሰለፍ ትግሉን ወደፊት ለማድረግ እኛ የግንቦት 7 ንቅናቄ አባላትና አመራር ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ ዛሬም ቁርጦ መነሳቱን በድጋሜ ቃል ይገባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## በጎዶሎ ተጫዋቾች የተጫወተዉ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ደጋፊዎቹን ሲያስጨፍር ዋለ

ከሰላሳ አንድ አመታት ቆይታ በኋላ ከአፍሪካ አቻዎቹ ጋር የተቀላቀለዉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ባለፈዉ ሰኞ ከፍተኛ ልምድ ካለዉና ከአምናዉ የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊ ከሆነዉ ከዛምቢያ ብሔራዊ ቡድን ጋር ተጫዉቶ አንድ ለአንድ በሆነ አቻ ዉጤት በመለያየት ኢትዮጵያ አሁንም የኳስ አርቲስቶች የሚኖሩባት አገር መሆኗን ለደቡብ አፍሪካና ለተቀረዉም የዓለም ህዝብ አሳይቷል። ብዙ የስፖርት ጋዜጦችና የእግር ኳስ ተንታኞች በጣም ዝቅተኛ ግምት የሰጡት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አንድ ተጫዋች በቀይ ካርድ ከሜዳ ወጥቶበትና 10 ለ 11 ተጫዉቶ የአምናዉን የአፍሪካ ሻምፒዮን አራዉጦ በአቻ ዉጤት ሲለያይ የተመለከቱ አሰልጣኞችና ጋዜጠኞች ሳይወዱ በግድ በኛዎቹ “ዋሊያዎች” ላይ ያላቸዉን ግምትና አስተያየት ለዉጠዉ የኢትዮጵያዉያንን የእግር ኳስ ችሎታ አድንቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከመክፈቻዉ ቀን ጀምሮ ከተደረጉት ጨዋታዎች ሁሉ ኢትዮጵያና ዛምቢያ ያደረጉትን ጨዋታ የተሻለ ፍክክርና ዘመናዊ የኳስ ስልት የታየበት ነበር ሲል ታዋቂዉ የደቡብ አፍሪካ “ሱፐር ስፖርት” ቴሌቪዥን ጣቢያ በተደጋጋሚ ዘግቧል።

የኢትዮጵያና የዛምቢያ ጨዋታ ከመደረጉ ከሁለት ቀን በፊት “ማሸነፋችን የተረጋገጠ ነዉና” የመጀመሪያዉን ጨዋታ ከኢትዮጵያ ቡድን ጋር መጫወታችንን ወድጄዋለሁ ብሎ የተናገረዉ ፈረንሳዊዉ የዛምቢያ ቡድን አሰልጣኝ 11 ለ 10 ተጫዉቶ ባለመሸነፉ እጅግ በጣም መደሰቱን ከጨዋታዉ በኋላ በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግሯል። በሌላ በኩል ደግሞ “ለመሆኑ በስም የሚታዉቅ የኢትዮጵያ ቡድን ተጫዋች አለ ወይ” ብሎ በቡድናችን ላይ ማፌዝ የሞከረዉ የእንግሊዙ አርሴናል ቡድን አሰልጣኝ አርሴን ዊንገር በተጫወተ ቁጥር የሚሸነፈዉን ቡድናቸዉን ከነማንቼ ጋር በአንድ ተርታ ማሰለፍ የሚችሉትን የአዳነ ግርማን፤ የሳላዲን ሰይድንና የአዲስ ህንጢሳን ስም “አይፓዳቸዉ” ዉስጥ ሲመዘግቡ አይተናል ሲሉ ብዙ ኢትዮጵያዉን ቀልደዉባቸዋል።

ጨዋታዉ የተጀመረዉ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ማጥቃት ሲሆን ሳላዲን ሰይድ 16ኛዉ ደቂቃ ላይ የዛምቢያዉን በረኛዉ አንሳፎ ወደ ላይ ከፍ አድርጎ የላካት ኳስ በአለም ዙሪያ የሚገኙትንና የብሔራዊ ቡድናቸዉን ጎል ማየት የናፈቁ ኢትዮጵአዉያንን ከየተቀሙጡበት ያስነሳች ግሩም የጎል ሙከራ ነበረች። ብዙም ሳይቆይ 24ኛዉ ደቂቃ ላይ ሳላዲን ሰይድ ከአዳነ ግርማ የተቀበለዉን ኳስ የሚመታ መስሎ አጠገቡ የነበረዉን ተከላካይ አታልሎ ሊያልፍ ሲል ተጠልፎ በመዉደቁ የጋቦኑ ዳኛ የሰጡትን የፍጹም ቅጣት ምት ዋሊያዎቹ ሳይጠቀሙበት አልፈዋል። የፍጹም ቅጣት ምቱ መሳት የልብ ልብ የሰጣቸዉ ዛምቢያዉያን በተከታታይ በግራ በኩል እያለፉ በተከላካዮቻችን ላይ ጫና ማድረግ ጀመሩ።

26ኛው ደቂቃ ላይ የዛምቢያው አማካይ ከመሃል ሜዳ ሰንጥቆ ያሳለፋትን ኳስ ለማግኘት፤ የዛምቢያው አጥቂና የዋሊያዎቹ በረኛ ጀማል ጣሰው ሲሻሙ ጀማል ከኳስ ውጪ በዛምቢያው አጥቂ ላይ አደገኛ ጨዋታ በመጫወቱ በቀይ ካርድ ከሜዳ ወጥቷል፡፡ የጀማል በቀይ ቀርድ ከሜዳ መዉጣት ልጆቻችን የነበራቸዉን የጨዋታ የበላይነት እንዳሳጣ በግልጽ የታየ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ በተከላካዮቻችን ላይ የተፈጠረዉን መረበሽ በመጠቀም የዛምቢያዉ ኮሊንስ እምቤሱማ ለአገሩም ለጨዋታዉም የመጀመሪያዉን ጎል አስቆጠሮ ትንሽ እንደተጫወቱ እረፍት ሆነ።

ከእረፍት በኋላ ብሔራዊ ቡድናችን የአሰላለፍ ለዉጥ አድርጎ በመግባት የብራዚሎቹን አይነት“ሳምባ ስታይል” አንድ ሁለት ቅብብል በተደጋጋሚ በማሳየት በስታዲዮሙ የተገኘዉ ተመልካች የሁለት ሺ አስሩን የአለም ዋንጫ ወደ ኋላ ዞር ብሎ እንዲመለከት አድርጎታል። ከእረፍት በኋላ 64ኛው ደቂቃ ላይ አዲስ ህንፃ፤ ሳልሀዲንና ሰይድና አዳነ ግርማ በአስደናቂ ሁኔታ ተቀባብለዉ ወደ ጎሉ የወሰዷትን ኳስ የእለቱ ኮከብ ተጫዋች ሆኖ የዋለዉ አዳነ ግርማ የዛምቢያን ተጫዋቾች አሞኝቶ በረኛዉ ባጠበበበት በኩል የመታት ኳስ የግራውን ቋሚ ብረት ተሳልማ ከመረቡ ጋር ተዋህዳለች። ስታድዮሙ በጩኸት ተሞላ፤ ዋሊያዎቹ ተቃቅፈዉ ሜዳዉ ላይ ተኙ፤ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ቴሌቪዥናቸዉ ፊት ጨፈሩ- ከ31 አመታት በኋላ የተገኘች ድንቅ ጎል ነበረች። ዳኛዉ ጨዋታዉን ለማስጀመር ፊሽካቸዉን ሲነፉ ኢትዮጵያዉያን ተመልካቾች የሚነፉት ቩቩዜላ ስታድዮሙ ዉስጥ የሚሰማዉ ብቸኛ ድምጽ ነበር ይህ የአዲስ ህንፃ፤ የሳልሀዲን ሰይድና የአዳነ ግርማ አንድ፤ ሁለት ሦስት ጨዋታና ዉጤቱ ለብዙ ኢትዮጵያዉያን የቀድሞዎቹን አንበሶቻችንን የሉቺያኖ ቫሳሎን፤የጌታቸዉ ወልዴንና የመንግስቱ ወርቁን ትዝታ ቀስቅሶባቸዋል።

የኢትዮጵያ ቡድን አቻ የሚያደርገዉን ጎል ሲያስቆጥር ከተመልካች ያገኘዉ ጭብጨባና ድጋፍ ጨዋታዉ ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ ሳይሆን አዲስ አበባ ዉስጥ የተደረገ አስመስሎታል። የእናት አገራቸዉን እዉነተኛ፤ ያልተበረዘና የጥንቱን አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ ባንዲራ ይዘዉ ለዋሊያዎቹ አንበሶች ቀኑን ሙሉ ድጋፋቸዉን ሲሰጡ የዋሉት ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ስደተኞች አንድ ሰዉ ለጎደለዉ ብሔራዊ ቡድናችን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በደል እንዴት ይራሳል? (ክፍል 1 )

የኢትዮጵያ ህዝብ መስከረምን ከጥቅምት ወይም ታህሳስን ከጥር ጋር አወዳድሮ ይህ ወር ከዚህ ወር ይበልጣል ወይም ይሻላል ብሎ የሚያምንበት ልዩ ምክንያት ባይኖረዉም እያንዳንዱ ወር በመጣ ቁጥር ግን ይዞት የሚመጣዉ የራሱ የሆኑ ታሪካዊ፤ ባህላዊና ፖለቲካዊ ትዝታዎች አሉት። የቅርቡንም ሆነ ቆየት ያለዉን ታሪካችንን ወደ ኋላ ዞር ብለን ስንመለከት ብሩህ ተስፋ የፈነጠቀልንና የዚያኑ ያክል ተስፋችንን አጨልሞ ጽልመት ዉስጥ የከተተን ወር ቢኖር ወርሃ ግንቦት ነዉ። አዎ ! . . . ግንቦት የፖለቲካና የባህል ቁመናችንን የዳሰሱ አያሌ ክስተቶችን ያስተናገደ ጉደኛ ወር ነዉ። . . . ግንቦት ልደታ፤ ግንቦት 8፤ ግንቦት 20ና ግንቦት ሰባት በየአመቱ የግንቦት ወር በመጣ ቁጥር የምንዘክራቸዉ አገራዊ ትዝታዎቻችን ናቸዉ። ግንቦትንና እነዚህን ትዝታዎች የብዕር ሰዎቻችን በየዘመኑ ያነሷቸዋል፤ የኪነት ሰዎቻችን ቅኔ ይቃኙላቸዋል የየዘመኑ የታሪክ ድርሳኖቻችንም ይዘግቧቸዋል።

ግንቦት 7 1997 በኢትዮጵያ ህዝብ የዲሞክራሲ ትግል ታሪክ ዉስጥ ልዩ ቀን ናት። ግንቦት ሰባት አንድ ትዉልድ ብቻ ሳይሆን ሁለትና ሦስት ትውልድ የደም ላብ አልቦና የህይወት ግብር ከፍሎ በረጂም ዘመን የትግል ታሪከትን መዝገብ ዉስጥ የጫራት አብሪ ኮከብ ናት። አዎ! ግንቦት ሰባት የዲሞክራሲ ትግላችን የከተባት ግዙፍ ክታብ ናት። ግንቦት ሰባት የ1940ዎቹ ትዉልድ አስቧት፤የ1950ዎቹና 60ዎቹ ትዉልድ አርግዟት የ1970ዎቹና 80ዎቹ ትዉልድ አምጧት የ1990ዎቹ ትዉልድ በጣር የወለዳት የኢትዮጵያ ህዝብ የበኩር ልጅ ናት። የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ያደረገዉ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የዘመናት የነፃነትና የዲሞክራሲ ረሀቡ ዉጤት፤የአርቆ ማስተዋሉ ምልክት፤ወይም ከዉስጥ ሆዱ የመነጨ የፍትህ፤ የነፃነትና የእኩልነት ፍላጎት ዉጤት ነዉ እንጂ የመላምት ታሪክ ቱልቱላዎች ሹክ ሊሉን እንደሚፈልጉት የወያኔ በጎ ፈቃድ ገጸበረከት አይደለም። ግንቦት ሰባት የአዋቂዉ መሳሳብ፤ የህፃናት መተሳሰብ፤የምሁሩ መናበብና የወጣቱ መተሳሰብ "ቱሉፎርሳ" ብሎ ከዘረኞች ጓዳ በገመድ ጎትቶ እዉን ያደረጋት የዲሞክራሲ ትግላችን ተምሳሌት የሆነች ቀን ናት።

ግንቦት ሰባት እዉን እንድትሆን አያሌ ኢትዮጵያዉያን የህይወት፤ የአካልና የንብረት መስዋዕትነት ከፍለዋል፤ አያሌ ቁጥራቸዉ በዉል የማይታወቅ ዜጎች ታስዋል፤ ተድብድበዋል ወይም ከአገር ተሰድደዋል። "ዲሞክራሲ ካለገደብ አሁኑኑ" ብሎ የጮኸዉ የ1970ዎቹ ወጣት በደርግ የቀይ ሽብር ወንጀሎኞች ካለርህራሄ ተጨፍጭፏል፤ ምሁሩ ካለፍርድ ተገድሏል፤ ወታደሩ ተረሽኗል እንዲሁም ብዙ ቤተሰብ ያለ አባትና እናት ተበትኖ ቀርቷል። ወርሃ ግንቦት በተለይ ግንቦት ሰባት እነዚህን ሁሉ ጀግኖች የምናስታዉስባት ቀን ናት። ግንቦት ሰባት በየአመቱ ስትመጣ ከምናስታዉሳቸዉ የቅርብ ግዜ ዉድ ሰማእቶቻችን ዉስጥ አንዱ ህጻን ነቢዩ ኃይሌ ነዉ።

ግንቦት ብዙ የሚተረክ ታሪክ፤የሚወሳ ወግና የሚነገር ገድል ያላት ወር ናት። የግንቦትን ጉድና ገድል አዉርተን እንጨርስ ብንል እየመሸ ይነጋብናል እንጂ የግንቦት ወግ ተነግሮ አያልቅም። ስለሆነም ዛሬ የምናወራችሁ ተነግሮ የማያልቀዉን የግንቦትን ታረክ ሳይሆን እቺ ጉደኛ ወር ካፈራቻቸዉ በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ ጀግኖቻችን ዉስጥ የአንዱን ሰማእት ታሪክ ነዉ። ለወትሮዉ የጀግኖቻችን ገድል ሲነገር ጀግናዉ ደጃዝማች ባልቻ፤ ወጣት ጀግኖቹ ዋለለኝ መኮንንና ማርታ መብርሀቱ፤ የሴት ጀግኖቹ ሸዋረገድ ሐይሌና እቴጌ ጣይቱ እየተባለ ነበር። ዛሬ የምናቀርብላችሁ የግንቦት ሰማእት ግን ደጃዝማችም፤ጎልማሳም፤ ወጣትም አይደለም። ህፃን ነቢዩ ሐይሌ ይባላል። ህፃኑ ጀግና ነቢዩ ሐይሌ እሱ ለራሱ በሚገባ ቀምሶ ያላጣጣመዉን የለጋ ህይወቱን ጣፋጭ መዐዛ እኛ ቋሚዎቹ እየሸተተን እንዲኖር የህፃንነት ለስላሳ ደረቱ በአግዓዚ አዉሬዎች ጥይት ተበጣጥሶ ህይወቱ ያለፈና የታሪካችን ምእራፍ አንዱ አካል የሆነ ህጻን ሰማእት ሲሆን በዛሬው ትረካችን በዚያን ወቅት ብሩህ ተስፋ ሰንቆ ይጠባበቅ የነበረ የህጻን ነቢዩ የእድሜ አቻ የትናንቱ ለጋ ህጻን የዛሬው የነጻነት አርበኛ ተስፋን የከተት ጥሪ ይዳስሳል።

ግንቦት 6 1997 ዓም ዕለቱ ቅዳሜ ነበር። ቅዳሜ የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን ነዉ። ሆኖም የዚያን ጊዜው ህፃን ተስፋ ቅዳሜን እንደ ሳምንቱ መጨረሻ ቀን አይደለም የሚመለከታት፤ ለተስፋ ቅዳሜ የእረፍቱ የመጀመሪያ ቀን ናት። ተስፋ አባትና እናቱ ኑሯቸዉ ሩጫ ነዉ፤ በአንድ በኩል አባቱ የተቀደደ ለመድፈን በሌላ በኩል ደግሞ እናቱ የተደፈነ ለመክፈት ጎንበስ ቀና እንዳሉ ነዉ የሚዉሉት፤ ስለሆነም ማታ ቤት ሲገቡ ሁለቱም አልጋቸዉ ላይ የሚወጡት በግዜ ነዉ። ተስፋ ግን ወላጆቹ ቴሌቭዥኑን ዝጋ ብለዉት እሱን ሳያስተኙ እነሱ እንደማይተኙ ያዉቃልና እቺን በግዜ መተኛት የሚሏት ነገር አይወዳትም፤ በተለይ አርብ ማታ። በ1997 ዓም በተለይም ከገናዉ ወር ከታህሳስ ጀምሮ ነቢዩ ቤታቸዉ ዉስጥ አንዳንድ ለዉጦችን መመልከት ጀምሯል። ለወትሮዉ በግዜ አልጋቸዉ ላይ የሚወጡት ወላጆቹ ትተዉት የነበረዉ ቴሌቭዥን ፊት መደርደር ጀምረዋል። ተስፋ የወላጆቹን መለወጥ ቢወድደዉም ምክንያቱን አያዉቀዉምና ግራ ግብት ብሎታል። አንዴ ከወላጆቹ ጋር ቁጭ ብሎ ቴሌቪዥን ሲመለከት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ እናቱን ያቅፋቻዉና ምነዉ አንቺና አባዬ አለወትሯችሁ ቴሌቪዥን ማዘዉተር ጀመራችሁ ብሎ ይጠይቃቸዋል። ትምህርት ቤት አይነግሯችሁም እንዴ! ዘንድሮኮ ትልቅ ምርጫ አለ ይሉታል እናቱ እጁን ይዘዉ ወደ ጉያቸዉ እየሳቡት። ት/ቤት ስልምርጫዉ በየቀኑ ነዉ የሚነግሩን ግን ምርጫዉንና ቴሌቪዥኑን ምን አገናኛቸዉ ይላቸዋል ፊቱን ወዳእናቱ አዞሮ አይን አይናቸዉን እየተመለከተ። አይ ልጄ! ቴሌቪዥን ላይ የምናየዉ ፉክክር፤እሰጥ አገባ፤ ሽሙጥ፤ ጉንተላና እንተ ትብስ አንተ ትብስ ክርክር ዘንድሮ የድፍን አበሻን ልብ ሰቅዞ ይዞታል። ይህ ምርጫ ደግሞ የዋዛ እንዳይመስልህ፤ የወያኔን የመጨረሻና የኢትዮጵያን ትንሳኤ መጀመሪያ የሚያበስር ምርጫ ነዉ።ደግሞም ከእኔና ከአባትህ በላይ ይህ ምርጫ የሚጠቅመዉ አንተን ነዉ ብለዉ እናቱ ንግግራቸዉን ሳይጨርሱ አባትየዉ ቀበል ያደርጉና . . . . አየህ ተስፋ ተቃዋሚዎች አሸንፈዉ ስልጣን ከያዙ ከአሁን በኋላ አገራችንን የሚመራት ጠመንጃ የተሸከመ ሀይለኛ ሳይሆን ህዝብ በችሎታዉና በባህሪዩ የመረጠዉ ዜጋ ብቻ ስለሚሆን እንተም እድገትህ አገር ከመምራት ጋር የተያያዘ ነዉ ብለዉ ወደ መኝታ ክፍላቸዉ ገቡ።

ተስፋ አልጋዉ ላይ ወጥቶ አይኑን እየጨፈነ ለመተኛት ቢሞክርም ቡና ሲጠጡ እንደዋሉ ባልቴት እንቅልፍ በአይኑ አልዞር አለ። ብንን ባለ ቁጥር አሁንም አሁንም ፊቱ ላይ እየመጣ የሚደቀንበት አባቱ "እንተም እድገትህ አገር ከመምራት ጋር የተያያዘ ነዉ" ብለዉ የተናገሩት ንግግር ነዉ። እኔም ኢትዮጵያን መምራት እችላለሁ እንዴ . . . . ብሎ ተስፋ እራሱን ጠየቀ። በአባቱ ንግግር ግራ ተጋብቶ ወይም የልጅ ነገር ሆኖበት አልነበረም ተስፋ ይህንን ጥያቄ የጠየቀዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ስልጣን የባለጠመንጃ ነዉና ተስፋ እንደማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ህጻን የአገር መሪ የመሆን ህልም ከምኞት ዝርዝሩ ዉስጥ የለም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምርጫዉን ካሸነፉ ግን ከዚህ በፊት ያልተመኘዉንና እሆናለሁ ብሎ ያላሰበዉን ማሰብና መመኘት ይችላል። አዎ! ተቃዋሚዎች ካሸነፉ ህፃን ተስፋ አድጎ አገር መምራት ይችላል። ብዙ ተንቆራጠጠ፤ አሰበ፤ አለመ. . . . ይበልጥ ባሰበና ባለመ ቁጥር "መሪ መሆን እችላለሁ" የሚል ሀሳብ በተደጋጋሚ መጣበትና የልጅነት አንጎሉ ይህንን ትልቅ ሃሳብ ማስተናገድ አቃተዉ፤ እሱም ቢሆን እዉነትም አንድ ፍሬ ልጅ ነዉና እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ። ሲነቃ ወላጆቹ እቤት ዉስጥ የሉም፤ ዬት እንደሄዱ ስለሚያዉቅ ተመልሶ ተኛ። ቀኑ ግንቦት ሰባት 1997 ዓም ነበር።

ተስፋ ከእንቅልፉ ተነስቶ የግድግዳዉን ሰዐት ሲመለከት የምሳ ሰዐት አልፏል . . . . . .አይመጡም እንዴ አለ ተስፋ መዘግየታቸዉ አስጨንቆት። ተስፋ ተቃዋሚዎች አሸነፉ ሲባል ለመስማት ቸኩሏል፤ ደግሞም የልጅ ነገር ሁሉንም በአንዴ ነዉና እናቱና አባቱ ሲመጡ ማን እንዳሸነፈ የሚነግሩት መስሎታል። አሁንም ቀና ብሎ ሰዐቱን ሲመለከት ከቀኑ ስምንት ሰዐት አልፏል። ወላጆቹ በቆዩ ቁጥር ተቃዋሚዎች የተሸነፉ እየመሰለዉ መቁነጥነጥ ጀመረ። የወያኔ ማሸነፍ የወደፊት እድሉን እንደሚያጨልም በዉል የተረዳዉ ተስፋ ሰዐቱ በጨመረ ቁጥር የእሱም ስጋትና ጭንቀት ጨመረ።

የቤታቸው ሰዐት ዘጠኝ ሰዐት ሆኖ ሲደዉል፤ ተስፋ ከእንቅልፉ ሲነቃና የቤቱ በር ሲከፈት እኩል ሆነ። ተስፋ ከተጋደመበት ፎቴ ተነስቶ "ማን አሸነፈ" እያለ ወደ በሩ ሲሮጥ ለግማሽ ቀን ቤቱን ሞልቶት የነበረዉ ዝምታ ተገፈፈ። አይ ልጄ! የኛ ስራኮ መምረጥ ብቻ ነዉ፤ ህዝብ የሰጠዉን ድምጽ ቆጥሮ ዉጤቱን የሚነግረን መንግስት ነዉ አሉት እናቱ እግራቸዉ ወደ ኩሺናዉ እየቀደመ። እንዴ! መንግስት ድምጽ ቆጥሮማ እንዴት ተቃዋሚዎች ያሸንፋሉ አለ እናቱን ተከትሎ ወደ ኩሺናዉ እየገባ። እናቱና አባቱ አይናቸዉ ሳያስቡት ገጠመና መልሱን በማያዉቁት የልጃቸዉ ጥያቄ ተገረሙ። የተስፋ እናት ባለሙያ ናቸዉ፤ ይህንን ደግሞ መንደሩ ሁሉ ያዉቀዋል። ኩሽና ዉስጥ እንደገቡ የጀመሩት ጥብስ ቤቱን አዉዶታል በእርግጥም የጥብሱ ሽታ እንኳን የተራበ ሆድ በልቶ የጠገበን አንጀትም ያስጎመጃል፤ ልጃቸዉ ተስፋ ግን የራበዉ ምግብ ሳይሆን የምርጫዉን ዉጤት ማወቅ ነበረና ሁሉንም ነገር ትቶ ከቴሌቪዥኑ ጋር ተፋጥጦ ቁጭ አለ።

(ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል)

## ፓሊሶች በአራት ኪሎ የሚገኙ ቤቶችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በኢትጵያ ውስጥ በልማት ስም እየተበራከተ የመጣውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አለማቀፍ ሰብአዊ መብት ተማጓች ድርጅቶች ችላ እንዳሉት ተመልክቷል። በአላማጣ ላለፉት አንድ ወራት የከተማው ህዝብ በልዩ ፖሊሶች ሲዋከብ እንደነበርመዘገባችን ይታወሳል። በአዲስ አበባ ላፍቶ ክፍለከተማ ቤታቸው የፈረሰባቸው በርካታ ነዋሪዎች አሁንም በከፍተኛ ችግር ላይ መሆናቸው ይታወቃል።

........................................................................................................................................................

## ፍሪዶም ሀዉስ ኢትዮጵያን ነጻነት ከሌለባቸዉ አገሮች ተርታ ፈረጀ

የአለማችን የነፃነት ድምጽ በመባል የሚታዉቀዉና "ፍሪደም ሀዉስ" በመባል የሚጠራዉ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በ2012 ዓም ባወጣዉ አመታዊ ሪፖርቱ ላይ ኢትዮጵያ ነጻነት ከሌለባቸዉ የአለማችን አገሮች አንዷ መሆኗን አሳወቀ። የአገሮችን የዲሞክራሲ ደረጃ፣ የፖለቲካ ነፃነትና የሰብዓዊ መብቶች አካባበር እያጠና በየአመቱ ሪፖርት የሚያወጣዉ ፊሪደም ሀዉስ የ2013 ዓም ሪፖርቱን ይፋ ሲያደርግ እንደገለጠው ኢትዮጵያ ነጻነትና መብት የሚደፈጠጥባት አገር ናት ብሏታል። ይህ ሰባ ሁለት አመት ዕድሜ ያስቆጠረዉና ተቀማጭነቱ አሜሪካ ዉስጥ የሆነዉ አለም አቀፍ ድርጅት ኢትዮጵያን ነጻነት የሌለባት የሰዉ ልጅ ሰብዓዊ መብት የሚረገጥባት አገር ናት ብሎ የፈረጀዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የወያኔ አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን ጨምሮ ሌሎች የሰብአዊ እና ፖለቲካዊ መብቶችን በየቀኑ ስለሚረግጥ ነዉ።

ፍሪደም ሐውስ ባለፉት ብዙ አመታት እንደሚያደርገዉ ሁሉ ዘንድሮም በአለም ዉስጥ የሚገኙ አገሮችን ነጻነት የሰፈነባቸው፣ ከፊል ነጻነት ያለባቸውና ጭራሽ ምንም ነጻነት የሌለባቸው አገሮች በማለት በሶስት ከፍሎ የተመለከተ ሲሆን ፣ ነጻነት የሌለባቸው አገሮች ብሎ ከፈረጃቸዉ የአፍሪካ አገሮች ዉስጥ ኢትዮጵያ፣ አንጎላ፣ ካሜሩን፣ ቻድ፣ ሁለቱ ኮንጎዎች፣ ጅቡቲ፣ ኢኳቶሪያን ጊኒ፣ ኤርትራ፣ ጋቦን፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ ቢሳው፣ ማሊ፣ ሞሪታኒያ፣ ሩዋንዳና ሶማሊያ ይገኙበታል። የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ በሚጠራዉ ክልል ዉስጥ ኬንያና ዩጋንዳ ከፊል ነጻነት የሰፈረባቸዉ አገሮች ሲሆኑ አፍሪካ ውስጥ ነጻነት የሰፈነባቸው ተብለው የተጠቀሱት አገሮች ቤኒን፣ ቦትስዋና፣ ኬፕ ቬርዴ፣ ጋና፣ ሌሶቶ፣ ማሊ፣ ሞሪሺየስ፣ ናሚቢያ፣ ሳኦቶሚና ፕሪንሲፒና ደቡብ አፍሪካ ናቸው።

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ግለሰቦችን በግፍ እያሰረ፣ እየገደለና ከአገር እንዲሰደዱ እያደረገ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊና ፖለቲካ መብቶች መከበራቸውን በተደጋጋሚ ቢገልጽም፣ የፍሪደም ሐውስ ሪፖርት በግልጽ የሚያሳየዉ ኢትዮጵያ በ2010 ዓም ከነበረችበት በከፊል ነጻ የሆኑ አገሮች ተርታ ወጥታ ነጻነት ወደ ሌለባቸው አገሮች ተርታ መውረዷን ነው።

## ወያኔ የእግር ኳስ ቡድናችንን የፖለቲካ መሳሪያ ማድረጉን እንዲያቆም ኢትዮጵያዉያን ስደተኞች ጠየቁ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከሚያደርስባቸዉ እስር፣ ድብደባና ግድያ አምልጠዉ ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ በስደተኝነት የሚኖሩ ኢትዮያዉያን ወያኔ የብሔራዊ ቡድናችንን በዘንድሮዉ የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፍ አስመልክቶ የፖለቲካ ድል ለማግኘት የሚያደርገዉን ዬትም የማያደርስ ሩጫ እንዲያቆምና ኢትዮጵያዉያን የዘር፣ የሐይማኖትና የፖለቲካ ልዩነት ሳያግዳቸዉ ለብዙ አመታታት ከአፍሪካ የእግር ኳስ ዉድድር ዉስጥ ጠፍቶ የሰነበተውን ብሔራዊ ቡድናቸዉን በጋራ እንዲደግፉ እንዲተዋቸዉ ጠይቀዋል። ስደተኞቹ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ወያኔ የአፍሪካ ዋንጫን አስመልክቶ ከዚህ አለም በሞት የተለየዉን የዘረኛ መሪዉን ፎቶግራፍ ያዘሉ ካናቴራዎች ለስደተኛዉ ለማደል ያደረገዉን ሙከራና ብሔራዊ ቡድናችን ደቡብ አፍሪካ ሲደርስ በአዉሮፕላን ጣቢያዉ የተገኘዉ በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ተጫዋቾቹን በአይኑ እንዳያይ የቡድኑን አባላት በአዉቶቡስ ደብቆ ወደ ሆቴላቸዉ ከወሰደ በኋላ ባወጡት መግለጫ ነዉ።

ብሔራዊ ቡድናችን ለዘንድሮዉ የአፍርካ ዋንጫ ዉድድር ካለፈባት ሰአት ጀምሮ የቡድኑን አኩሪ ዉጤት ከዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ራዕይና ከወያኔ የእድገት ፖሊሲ ጋራ ማያያዝ የጀመሩት የወያኔ መሪዎች ቡድኑ ከ31 አመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ዉድድር ያለፈዉ በወያኔ ጠንካራና ብልህ አመራር እንደሆነ ተናግረዋል። የግንቦት ሰባት ድምጽ ሬድዮ ይህንን የወያኔ አባባል አስመልክቶ የጠየቃቸዉ አንድ የዋሺንግተን ዲሲ ነዋሪ እንደተናገሩት ወያኔ ከራሱ ዉጭ ማንንም የማይሰማ ደንቆሮ ስለሆነ ነዉ እንጂ ብሔራዊ ቡድናችን ከትልቁ የአፍርካ እግር ኳስ ዉድድር ተለይቶ ከቆየባቸዉ 31 አመታት ዉስጥ ሃያ አንዱ አመታት የራሱ የወያኔ አመታት ናቸዉ፤ እንድያዉም ባለራዕይ የተባለዉ መሪ ሃያ አንድ አመት ሙሉ አገራችንን ሲመራ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ዋንጫ ላይ ሳያያት ነዉ ከዚህ አለም በሞት የተለየዉ ብለዋል።

እኚሁ የኢትዮጵያን አግር ኳስ ቡድን ከ3ኛዉ የአፍሪካ ዋንጫ ጀምሮ የሚያዉቁት ኢትዮጵያዊ ንግግራቸዉን በመቀጠል ደርግ የሚወደስ መንግስት ባይሆንም በደርግ ዘመን ኢትዮጵያ 10ኛዉን የአፍሪካ ዋንጫ ያዘጋጀች ሲሆን በ1974 ዓም ሊቢያ ዉስጥ በተደረገዉ ዉድድር ተሳታፊ እንደነበረች ተናገረዋል፤ ከዚህ በተጨማሪ በደርግና በኃ/ስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ በዘጠኝ የአፍሪካ ዋንጫ ዉድድሮች የተሳተፈች ሲሆን ሦስት አፍሪካ ዋንጫ ዉድድሮችን አዘጋጅታ አንዱን አሸንፋላች ብለዋል። ወያኔ በዘንድሮዉ የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፋችንን እንደራሱ ድል የሚወስደዉ ከሆነ የኢትዮጵያን እግር ኳስ ታሪክ ዞር ብሎ መመልከት ይኖርበታል ካሉ በኋላ ብሔራዊ ቡድናችን የወያኔ ወይም የወያኔ ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ኢትዮጵአዊ የሚወክል ነዉና ወያኔ ይህንን አገር ቤት የለመደዉን አስቀያሚ የመለያየት ፖሊቲካዉን ትቶ ስፖርትን በስፖርተነቱ ብቻ እንዲመለከት በመጠየቅ አስተያየታቸዉን ጨርሰዋል።

## በጎዶሎ ተጫዋቾች የተጫወተዉ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

አስራ አንደኛዉ ሰዉ ሆነዉት ዉለዋል። የወያኔ ባለስልጣኖች ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ብሔራዊ ቡድናቸዉ ደቡብ አፍሪካ ሲገባ አቀባበል እንዳያደርጉለት ቢያደርጉም ጉዳያቸዉ ከወያኔ ጋር ሳይሆን ከአገራቸዉ ብሔራዊ ቡድን ጋር መሆኑን በሚገባ የተረዱ ኢትዮጵያዉያን በስታድዮሙ የተገኘዉን ተመልካች "ድጋፍ ማለት" እንደ ኢትዮጵያዉያን ነዉ እንዲል አስገድደዉታል። የግንቦት ሰባት ድምጽ በዚህ አጋጣሚ ለብሔራዊ ቡድናችን ያለዉን ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍ እየገለጸ ለቡድኑ መልካም ዉጤት ይመኛል።

### መቼ ይሆን ማብቂያው!!

በጨለማው ዘመን፣ በአስራ ሰባቱ
የሰው ዘር ተዋርዶ፣ በሆነበት ከንቱ
በግፍ የተሞላ፣ ነበር ግርፋቱ።
በዚህ የተነሳም፣ ሽብር በማየሉ
መውጫውን ዘይደል፣ ሁሉም በየቅሉ።

አብዛኛው ተይዞ፣ በፍርሃት ቆፈን
ከሁሉ አስበልጦ፣ አድሮ መገኘቱን
ብሶቱን አምቆ፣ አቀርቅሮ አንገቱን
ሊያሳልፍ ሞክሯል፣ ንፋሱን ወጀቡን።
በጣም የባሰበት፣ እጅጉን የሰጋም
ይህንን መከራ፣ ያለ አላይ አልሰማም
በቅታው ይቺ ዓለም፣ ገብቷል ወደ ገዳም።

የደነበረውም ሜዳውን አቋርጦ፣ ተራራውን ወጥቶ
ቁልቁለቱን ወርዶ፣ ወንዙንም ተሻግሮ
ፊቱንም ሳያዞር፣ ሳያሰማ ሮሮ
ኮብልሏል ከአገር፣ እልም ብሎ ጠፍቶ።

ብርታቱን ያገኘው፣ አሰምቶ ፉከራ
እያለ ወደፊት፣ ፋኖ ተሰማራ
ሊባጀን በደሙ፣ ከሳት ከመከራ
ውሃ አንጠልጥሎ፣ ባንዲት ትንሽ ኮዳ
ብረቱን አንግቦ፣ ወ'ቷል ወደ ሜዳ።

ጥቂት የማይባል ምውት፣ ለሲጋው የራራ
የዛ ወገኑን፣ አ'ርን ባላጋራ
በፍጹም ዘንግቶት፣ እራሱ መሆኑን ነገ ባለተራ
ባንድ አልጋ ተኝቷል፣ ከጨቋኞች ጋራ።

ጊዜው ደረሰና፣ የግፍ ዋንጫ ሞልቶ
ከውስጥም ከውጭም፣ ተንጦ ተገፍቶ
ይመስል የነበረው፣ የተሳሰረ ድር
ሆኖ የእምቧይ ካብ፣ የድቡሽት ላይ ክምር
ሲወድቅ ሥርዓቱ፣ ላይገኝ ቅሪቱ
መድረሻው ጠፍቷቸው፣ ደቀመዛሙርቱ
እንደ ጉም በነኑ፣ ጠፉ ተበተኑ
አይደለንም ብለው፣ ከዱ በጭፍኑ።

ወንበር የነጠቁት፣ አዲሶቹ አንጋቾች
ስንጠብቃቸው ይሆናሉ ብለን፣ መድህን ቤዛዎች
ሳይውሉ ሳያድሩ፣ ገልጠው አሳወቁን
ጽንስ መሠረቱ መተዳደሪያቸው፣
ከአራዊት መሆኑን።
ከፋፍለው ሊገዙን፣ በዘውግም ከለሉን
ከላይ ከመለኮት የተቀበልነውን፣
በኃይልም ገፈፉን ነጻነታችንን
ሊያስረሱን አስበው፣ ሰው መሆናችንን።

መቅተል የለመዱ፣ ሰውን ማንገላታት
መግረፊያው ልምጩ፣ ያለፈው ሥርዓት
ተቆራርጦ ሲወድቅ፣ በአንክሮት ስላዩት
ቆርጠው ተነስተዋል፣ ብለው ጥጃ ጨንገር
ልጡ አለንጋ'ሚሆን፣ እንጨቱ ሲሰበር
በዚህ የተገኘ፣ አቤት ያለ አሳር
ያደማል አለንጋው፣ የእንጨቱን ሰንበር።
እንዲያው በደፈናው፣ ማለቱ ይቀላል
ግፍና መከራው፣ ከሯል ተባብሷል
ሦስት ትውልድ ባንደ'ዜ፣ ማስለቀሱን ይዟል።

ምን ያመጣ ይሆን፣ መጻኢ ዕድላችን
ሲሆን የኛ ነገር፣ እንዲያው ቁጭ ብሎ መናፍቅ ያለፈን
ከማንሳት ቀንበሩን፣ በግድ በላያችን
የተጫነብንን።

በዋለልኝ እግዜር
ዋሺንግቶን ዲ.ሲ

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፦ በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>፦ በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፦ ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org